በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ታሕሳስ 27 ቀን 2011
አዲስ አበባ
ጋዜጣዊ መግለጫ

# 60ኛ መደበኛ የካቢኔ ዉሳኔዎች

የሚኒስትሮች ም/ቤት ታሕሳስ 27 ቀን 2011 ባካሄደው 60ኛ መደበኛ ስብሰባ በአስር የተለያዩ ስምምነቶችና በማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

ም/ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተዘጋጅተው በቀረቡት የስምምነት ሰነዶች እና የማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆች ላይ ሲሆን ስምምነቶቹ:

- በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በህንድ ሪፐብሊክ የተደረገውን የመረጃ እና የመገናኛ ብዙኃን ስምምነት፣
- ከኮትድቯር ሪፐብሊክ የዲፕሎማቲክ እና ሰርቪስ ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት የተደረገውን ስምምነት፣
- ከቬንዙዌላ ቦሊቫሪያ ሪፐብሊክ በባህል ዘርፍ ትብብር ለማድረግ የተደረገውን ስምምነት፣
- ከጋና ሪፐብሊክ በኮሙኒኬሽን ኢንፎርሜሽን እና በሚዲያ ዘርፍ የተደረገውን የትብብር ስምምነት፣
- በሞንተሪያል ፕሮቶኮል ላይ የተደረገውን የኪጋሊ ማሻሻያ ስምምነት፣
- በስዊስ የፌዴራል ምክር ቤት በመርሃ ግብር የሚከናወን መደበኛ የአየር አገልግሎቶች ስምምነት፣
- እንዲሁም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መካከል የተደረገውን የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት

የተፈረመውን የመግባቢያ ሰነድ፣ የኢንቨስትመንት ማስፋፊያና ጥበቃ ስምምነት እና የሥራ ስምሪት የመግባቢያ ስምምነት ለም/ቤቱ ቀርበው ውይይት ከተደረገባቸው በኋላ ስምምነቶቹ ለአገራችን የሚያስገኙትን ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ም/ቤቱ ረቂቅ አዋጆቹን ተቀብሎ ይጸድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡

//